# የግንቦት 7 ምሁራን ተከታዮችና ጋዜጠኞቻቸው ከኤርትራዊያን የቀሰሙት "ውሸትን የማግዘፍ!" አዲስ ትምህርት!

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ/Ethiopian Semay)

getachre@aol.com

በዚህ ጥቅስ ልጀምር "በአንድ ወቅት ያነበብኩት የአንድ ምሁር ጽሑፍ "ታሪክ ትምህርት ቤት እንጂ ፍርድ ቤት አይደለም" የሚል ጽሑፍ አንብቤ ነበር። እርግጥም ታሪክ ትምህርት ቤት ነው። ባለፉት የተፈጸሙት ስሕተቶች ላለመድገም የሚያስችሉ ተሞክሮዎችን የምናገኝበት ት/ቤት ነው።" ጦቢያ መጽሔት ላይ ከታሪክ አምዳችን ላይ ቀርቦ ከነበረው ጽሑፍ የተወሰደ። የመጽሔቱ ገጽ ኮፒ ተደርጎ ከአገር ስለተላከልኝ የጸሓፊው ስም በከፊል ፊደል ተቆርጣል አይታይም።

ከጸሐፊው በከፊል እስማማለሁ፤በከፊል አልስማማም። ታሪክም ዳኛ ሆኖ 'ታሪክ' በተባለ ችሎት ፍርድ ይፈርዳል።"ታሪክ ይፍረደን" የምንልበትም ለዚህ ነው። ሆኖም በአንደኛው አባባላቸው ተስማምቻለሁ። ታሪክ "ትምህርት ቤት" የመሆኑ ግን እውነት ነው። ዛሬ እዚህ ውጭ አገር የሚኖሩ ምሁራንና ጋዜጠኞች የተባሉት በቀለም ትምህርት ከባችለር እስከ ዶክተር ማዕረግ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን የሚያመልኳቸውን የግንቦት 7 መሪዎቻቸው በቅርቡ በየድረገጾች የሚጽፉዋቸው አስተያየቶች እጅግ የሚገርም ነው። ድሮም ያው ቢሆኑም ሰሞኑን ግን ብሶባቸዋል። የዛሬ ልዩ የሚያደርጋቸው አዲሱ ባሕሪያቸው "ውሸትን አግዝፎ" በማስተጋባት ኤርትራዊያን ጸሐፊዎችን በእጥፍ የመቅደማቸው ክስተት ነው ።

እንደሚወራው ከሆነ "አቶ ካሳ ከበደና ሻለቃ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስን" (አባሎች ናቸው ይባላል) ጨምሮ የቀሩት 11 የግንቦት 7 አማራሮችና እሳት ውስጥ የተሰገሰጉት የግንቦት 7 ጋዜጠኞች ከመሪዎቻቸው ጋር ከመመረሽ የተቆጠቡ ቢሆኑም፤ ሰሞኑን ብርሀኑ ነጋ እና ንአምን ዘለቀ ወደ 'ምድሪ ባሕሪ' ከዘለቁ ወዲህ ድሮ ጦርነት ከፍተው በቅርቡ በዚህ ወር ምንሊክ ቤተመንግሥት/አዲስ አበባ እንደሚገቡ የጻፉላቸው ጸሐፊዎች አንብቤአለሁ (ብርሃኑ ለፋሲካ ወያኔን አውርጄ አዲስ አበባ ይገኙችሁ እገባለሁ ብሎ ንግግር እንዳደረገው ማለት ነው፡ ከ 5 ዓመት በፊት)።

ዘሐበሻ ድረግጽን ብትጎበኙ አብዛኛዎቹ እንዲህ ያሉ ጽሑፎች እና ንግግሮች ታገኛላችሁ፤"በአውድዮም" ታደምጣላችሁ። ከዚያ ቀጠና ባሻገር "ስሜት" በሚባል "ጭራቅ" እየተገረፉ "እንደዛር የሚጮኹ" በየፓልቶክ መድረኮችም ታገኙዋቸዋላችሁ (አንድ የለየለት የግንቦት አዳማቂና በሆያ ሆየ ስሜት የተያዘ ጥሩ የእንግሊዝ ቋንቋ ጸሕፈት ችሎታ ያለው ምሁር፤ እኔ በማከብረው በአሲምባ ድረገጽ ላይ ጽሑፉን ሲለጥፍ  የብርሃኑ ነጋ ወደ አስመራ መዝለቅ ኢትዮጵያዊያን ከጣሊያኖች ጋር የገጠምንበት ወደ ዘመቻ የመትመምና ድል የመታንበት ታሪክን በማመሳሰል ጽፏል። እንዲህ ይላል፤

"The children of Ethiopia are once again on the move. Our fathers and mothers marched north to resist fascism. We their children are marching south to clean the fascist remnants that stayed behind. We surprised the whole world the first time around and there is no reason to think it would be any different this time."

"Today all Ethiopians are angry at the children of Askaris that have out lived their welcome. We are hearing gunshots from the north. We are witnessing the joy of our people in the motherland and all over the world where we have been scattered by Woyane. Except for Woyane and their puppies I have not met a single Ethiopian that is not happy with the final decision to deal with the varmints once and for all. "

ጸሐፊው ይልማ በቀለ ይባላል። ይኽ ሁላችንም ሆነ አገራችን የሚያሳስባት "የስሜት" ዕብደት ነው። እያንዳንዱ አረፍተነገር ብተነትን ጸሐፊው ከሚያገዝፈው ውሸት አኳያ  ሰፊ ትንተና ስለሚወስድብኝ ትንተናውና ትዝብቱ ለናንተ ልተወው። ከኢሳያስ አፈወርቂ የባሰ "በአስካሪስነት/በጣሊያን ወታደርነት/ባንዳነት" የሚታማ በታሪካችን ከቶ መቸም ተፈልጎ አይገኝም።ሆኖም ጸሃፊው "ይልማ በቀለ" እልል እያሰኘው ያለው ከትልቁ የአስካሪሶቹ ቁንጮ ከኢሳያስ ጋር ተጠግቶና ታጥቆ "ደቡብ" ድረስ የተበተኑትን ርዝራዥ "አስካሪሶችና" "ቨርመንቶች/ተባዮች/ነቀዞች/አምበጦችን(?)" ለመደምሰስ ወላጆቻችን ከወራሪ ጣሊያኖች ጋር ካደረጉት ከዓድዋው ጦርነት ጋር ማመሳሰሉና በብርሃኑ ነጋ እየተመራ ያለው
ጦርነት ዓለም በተአንክሮ እያየ መሆኑን የተማሩት ክፍሎች ሲነግሩን፤ እውነትም የኤርትራ ምሁራን ትንሿን ነገር አግዝፈው የመዋሸት ተላላፊ በሽታቸው የኛዎቹ የኢትዮጵያ ምሁራንም ጭምር እንደተጋባባቸው ማስተዋል እንችላለን።

ቤት ንብረቴን ሳይል ከየአቅጣጫው ወደ ዓድዋ የተመመው አርበኛ ከ50 በላይ ከማይሞሉ የግንቦት 7 ታጣቂዎች፤ያውም ከፈሎቹ ያልጠበቁት ፋሺስታዊ ግርፋትና ሞት ስላጋጠማቸው በድንጋጤ እየሸሹ እየተመለሱ እያየን፤አንዳንዱም ማምለጫ አጥተው በሃይል ተይዘው ካምፕ

ውስጥ እና ከሻዕቢያ “የእርሻ ልማትና ቁፋሮ” በረሃ ላይ በንዳድ በሽታ እየተሰቃዩ የሚገኙ ምስኪን ዜጎቻችን (ብሔራዊ ግዳጅ ተብለው ኤርትራኖች ሳዋ ላይ መውጫ አጥተው እየተንገላቱ እንደሚገኙት ማለት ነው) ያሉበትን ሁኔታ እያወቅን ይህ አሳዛኝ ክስተት ምሁራን ነን የሚሉን ከዓድዋ ዘመቻ ጋር ሲያነጻጽሩት አገሪቷ የቀለም/ የአካዳሚ ትምህርት የተማሩ ዜጎች እጥረት ሳይሆን “የሚታዩ ነገሮችን የሚያገናዝብ አርቆ አስተዋይ የምር ምሁር” በብዛት ያለመውለድዋ እጅግ ያሳዝነኛል።

ጸሓፊው በጽሁፉ ላይ፤ ግምቦት 7ን የሚቃወም ሁሉ ‘ወያኔና አሽከሮቻቸው” እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም የሚል ድምዳሜ ደርሷል። እኔና መሰል ዜጎች ግንቦት 7ን እንቃወማለን። ግን ወያኔዎች አይደለንም። በመቃወማችን እኛንም ወያኔና የወያኔ አሽከሮች አድርጎ አስቀምጦናል (በዚህ መልክ የአስካሪስ ልጆች ነን ማለት ነው)።

የግንቦት 7 ቁንጮው ጋዜጠኛ “ሲሳይ አገና” ሕብር ራዲዮን ከተባለው ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቁ እንዳለው ‘ካለ እኛ ሌላ ኢትዮጵያዊ የለም የሚሉ ክፍሎች ሞልተዋል’ ፡ “የግንቦት 7 መሪዎችን ጥሩ ኢትዮጵያዊነት የሚጠራጠር ከቶ የለም፡፤ ካሉም ወያኔዎች ናቸው።”፤ “ጥሩ ኢትዮጵያዊነታቸውና ማንነታቸው ከማሕደራቸው ከቅንጅት ጊዜ ጀምረው እስካሁን ድረስ ለሕዝባቸው በመታገል አስመስክረዋልና”፤ ብሏል አቶ ሲሳይ አገና።

የነ ብርሃኑ እና የነ አንዳርጋቸው የትግል ማሕደር መቸም ለምናውቅ ሲሳይ ሊያሞኘን አይቻለውም።ብርሃኑነ ነጋ እና ስየ አብርሃ እስር ቤት ሆነው በውድቅት ሌሊት “አንድ እስረኛ ሲገረፍ ሲጮህ ሰምተው፤ ብርሃኑ “የነጻነት ጎህ ሲቀድ” በተባለው መጽሐፉ የነገረንን እዚህ ልጥቀስ። ወደ ጥቅሱ መግባቤ በፊት “ሰቆቃ /ቶርቸር/ የለም እያለ ያገኘውን ፈረንጅ ይናገር ነበር። እንዲህ ይላል፡-

“እስር ቤት አንደገባን ሌሊት ላይ የተደበደበ ሰው ጩኸት እንሰማ ነበር። በመጀመሪያ ማመን ነበር ያቃተን። ሰቆቃ (Torture) በኢትዮጵያ የለም ብልን እናምን ስለነበር፤ ጭኸት ስንሰማ ግራ ተጋባን። እነ ስዬ ከመጡ በኋላ እንደዚሁ አንድ ሌሊት ይህን የሰው የስቃይ ጩኸት ስንሰማ አድረን ጠዋት ስዬን ‘ሰማኸው ወይ የማታውን’ ስለው፤ እሱም ‘መስማቱንና ማመን እንዳቃተው፤ እንደዚህ ዓይነት ነገር እንዳለ እንደማያውቅ ነገረኝ። “ይህ ነው እንግዲህ የታገላችሁለት” ብዬ እንደ ቀልድ ጣል አደረግኩ” *(የነፃነት ጎህ ሲቀድ ፡ ገጽ 199)*

ሲሳይ እየነገረን ያለው ብርሃኑ ነጋ ወያኔዎችን አንደታገለ፤ ወያኔን መሰሪ ጠንቅቆ የሚያውቅ ታጋይ ኢትዮጵያዊ አድርጎ ነው በቃለ መጠይቁ እየሳለው ያለው። ብርሃኑ ቢያንስ እዛው ከወያኔዎች ጋር ዊስኪ ሲጨልጥ፤ መለስ ጋር ከበረከት ጋር ከታምራት ጋር ሲሳሳቅ ሲዝናና ከ7 አመት በላይ አብሮ አሳልፏል።

አብሮ  ከወያኔዎች ከነመለስ ጋር በእፍ-እፍ ፍቅር ሲያስልፍ ሕዝቡም ልክ እንደ እርሱ በምቾት የሚኖር፤ ማንም የማይነካው፤ ያለ ስጋት 'ዊስኪ' እያስጠጡ የሚገዙት መስሎት ከወያኔዎች ጋር በኩራት እና ያለስጋት ሲኖር እንደነበር የማናውቅ መስሎት ሲሳይ አገና ስለ ብርሃኑ ረዢም ታጋይነት ማሕደሩን ለማቆነጃጀት ሞክሯል። ያውም እኮ በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ወያኔ እና ሻዕቢያ የሰጡትን ኤርትራን የነጠለ የኢትዮጵያ ካርታ ለተተኪው ትውልድ ያስተላለፈ ሰው እኮ ነው፤ የረዢም ጊዜ ታጋይ እያለ የሚቀባባው።

ጋዜጠኞች ማወቅ ያለባችሁ፤ እኛም እንደናንተው አማርኛውን ማታፈጥ ባንችልበትም፤ ሁኔታዎች አንከታተላለን። የግንቦት 7 አመራሮች ጥሩ ኢትያዊያን ናቸው፤ ያገራቸው ታሪክና ሉአላዊነት ያስከብራሉ እያላችሁ ለምትዘባርቁ እንደ ሲሳይ አገና የመሳሰላችሁ ጋዜጠኞች ሁሉ፤ ይህ ከዚህ በታች ያለው ምን ትሉታላችሁ?

የግንቦት 7 አመራሮችን የነ ኤፍሬም ማዴቦ ንግገሮችና ጽሑፎችን መርምሩ። "መለስ ዜናዊ እና አፄ ምንሊክ ኮሎኒያሊስቶች ናቸው" ብሎ የነገረንን ጸረ አማራነትና ስለ ኤርትራ ሉአላዊነት ጥብቅና መቆማቸውን፤ በገሃድ ሲናገሩ፤ ለሲሳይ አገና "ጥሩ ኢትዮጵያዊነት" ማለት ያ ነው። (ከላይ ለሚታየው ፎቶግራፍ ምንጭ አሲምባ ድረገጽ ላይ የተለጠፈ ሲሆን ለፎቶው ባለቤት ምስጋና አቀርባለሁ)

ሲሳይ የ "ነፍጠኛ" ነገድ ስላልሆነ የግንቦት መሪዎች ተወካይ/ የግንቦት 7 ሕዝብ ግንኙነት ተጠሪ የሆነው ኤፍሬም ማዴቦ "ነፍጠኞችን" ቢዘልፉና "ነፍጠኞችን በቁጥጥ ስር አስገብተንላችኋል" ብለው ለኤርትራዊያኖች በፌስቲቫላቸው ሄደው ሲያረጋጋጡላቸው መስማት "ነፍጠኛ" እየታበለ ያለው ክፍል ለሲሳይ ምኑም ስላልሆነ፤ እንዲህ ያለው "ዘለፋ እና ባንዳነት" ለሚየስተጋቡ የግንቦት 7 አመራሮች፤ ለጋዜጠኛ ሲሳይ አገና፤ እንዲህ ያለ

አማራን የሚዘልፍ ንግግርና አገርን ዝቅ የሚያደርጉ የግንቦት 7 ፖለቲከኞች፤ በሲሳይ አገና ግምገማ “ጥሩ የኢትዮጵያዊነትና የታጋይነት” ተምሳሌት ንግግሮች መሆናቸውን ያምናል።

ይልማ በቀለም ግንቦት 7ን የሚቃወም ሁሉ “ወያኔ” ነው ብሎ ደምድሟል። ልክ ዘሐበሻ ላይ የምትሞነጫጭር ሥርጉት ምንትስ ነኝ የምትል ጸረ ትግሬ የሆነች “በኢሰፓአኮነቷ” ሳታፍር የምትኩራራ **‘አብሾ’**፡የሆነች ሴት፤ ጌታቸው ረዳ “ወያኔ” ነው ብላ እንደወነጀለቺኝ እና ወያኔዎች ደግሞ በይልማ በቀለ አገላለጽ “ቨርመንቶች፤እና የአስካሪስ ልጆች” ናቸውና፤ ግንቦት7ን የሚቃወም ሀሉ “ቨርመንቶችና የአስካሪስ ልጆች” አድርጎ ለጥፎብናል።

በጣም ሚገርመው ደግሞ፤ ከታሪክ የማይማሩ እነኚህ ክፍሎች፤ብርሃኑ ሄዶበታል ተብሎ እልልታ እያስሰሙን ባለበት መሬትና ጫካ ያለፉ በተሞክሮ ያዩት ሰዎች በቀናነት ምክር ለሚያስጠነቅቋቸው እንኳ ሳይቀር “እየዘለፏቸው” ይገኛሉ። ኤርትራ ድረስ ሄደን ጦር አዘጋጅተን ለመዋጋት ዝግጁነታችን ብናሳይም፤ ኢሳያስ አሽከሮቹን እነ ኰለኔል ፍፁምን መሳይ አረመኔዎችን አሰማርቶ በእነሱ ሥር ትዕዛዝ እንደረንታዘዝ አድርጎ መላወሻ አሳጥቶን፤ ወንድሞቻችንን አሳስሮ ገድሎብን ተስፋ ቆርጠን ተመልሰናል፤ በዛው ጦርንት ለማካሄድ መሞከር “ዕብደት” ነው፤ ከእኛ ልምድ ተማሩ፤ ብለው አንድ ብቻ ሳይሆን በጣም በርካታ ታጋዮች እና መሪዎች እንዲሁም እቦታው ድረሰ የሄዱ ጋዜጠኞች ሁሉ ስለታዘቡት ገጠመኝ እያስረዱ በምስክርነታቸው እያስጠነቀቁዋቸው ባለበት ጊዜ ነው፤ እነ መሳይ መኮንን እና እነ ፋሲል የኔአለም የመሳሰሉ የኢሳት-ግንቦት ጋዜጠኞች ደግሞ የሚነግሩን የቅጥረኛነት ራፖር ሲዘግቡ ታዝበናል።

ዳዊት የተባለው የሻዕቢያ ሻለቃ ጎምበስ ብሎ ሙቅ ውሃ አዘጋጅቶ እግሬን ሊያጥበኝ ሞክሮ ነበር፤እንደዚህ የመሳሰሉ የዋሃን ሻዕቢያዎን “በነብሰ ገዳይነትና ገራፊነት” የሚስሏዋቸው ውጭ አገር ያሉ ሰይጣም ተቃዋሚዎች እንጂ ኤርትራኖቹ መላእክት ናቸው፤ዘፈናቸው ከተማዎቻቸው፤ የፊያሜታ ሽሩባዎች፤ የጥርሳቸው፤የአቀባበላቸው በየግድግዳው የተለጠፉት ባንዴራቸው ማማር፤ ሰርጋቸው፤ የአማርኛ እስክስታቸው፤“ውይ ስያምር!” እያሉ በቪዲዮ “እዩልን እዩልን” ፖለቲካ ሲሰሩብን ቆይተው፤ ዛሬ ደግሞ እነኚህ ምሁራንና ጋዜጠኞች የሚባሉት ቀደም ብሎ የተፈጸሙ ስሕተቶችን ካለፉት ኤርትራ ሄደው የታገሉ ታጋዮችና መሪዎች ማስጠንቀቂያ ሳይማሩ ከነሱ ጋር “እሸሸ ገዳሆ!” እንድንጨፍር ጥሪ እያደረጉልን ናቸው።

እስክስታው፤ በሞቀ ውሃ እግር ማስታጠቡ መልካም ነው፤ ግን የኋላ ኋላ “ኣይበልናንዶየ፤ ኣይበልናንዶ!” (“እኛስ ብለን ነበር” የሚለው ከልቤ ዛሬም የምናፍቃት ከዚህ ዓለም የተለየች የመጀመሪያ የወጣት ዕደሜ እጮኛዬ የመነን ስቡሕ ወንድም የጠርጠራው (ገብረምደህን ስቡሕ) የባድሜው ዘፈን በድጋሜ ቢዘፈን ሃላፊነቱ የምሁራኖቹ እና ጋዜጠኞች እንጂ የማንም ሊሆን አይችልም)።

ይበልጥ አሳዛኝ የሚያደርገው ድግሞ፤ ያ ሁሉ ተሞክሮ ያላቸው ሰዎች ምክር እየናቁ፤ የግንቦት 7 መሪዎች ዛሬም እዛው ድረስ ሄደው ምሲኪን ታጋዮችን በኤርትራ ነብሰበላ ገራፊዎች እጅ እያስደበደቡ፤ወፌ ላላ ተሰቅለው ሰቆቃ/ቶርቸር ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርጉ፤ በሰው ህይወት የሚጫወቱ ቁማርተኞች/ወንጀለኞች ዛሬም ያንንኑ በመድገም ላይ ናቸው። ከኤርትራኖች ጋር ተመሳጥረው ይህን ጉድ የሚፈጽሙ የግምቦት 7 መሪዎችና የድርጅታቸው አካሄድ "ባትደግፏቸውም፤ አትቃወሙዋቸው" የሚሉ ሸምጋይ/ደላላ ጋዜጠኞችም አሉ። ባብዛኛው የተካኑ ጋዘየጠኞች በጓደኛነትና በቡድነተኛነት ማሕበር እንደ ዘመድ አዝማድ ስለተያያዙ ስለተያያዙ፤ እየተደረገ ያለው ወንጀል በነሱ መሃል የሚፈጸም የጋዜጠኛነት ሙያ የማይወደው ስነ መግባር/ኤቲክስ እርስ በርስ እየተሸፋፈኑ ትግሉን ጎድተውታል። አንድ ጥሩ ጋዜጠኛ ያየሁ "'ደምስ" የተባለው ጋዜጠኛ ነው፤ በድፍርት ሲጋፈጣቸው እያየሁ ያለሁት። አንድ ብቻውን መንጋ ቡድንተኛ ጋዜጠኛን ብቻውን ቢጋፈጣቸው ስንቱ ጋር ይደረስሳል (ሌሎች ያላስዋልኳቸው ሊኖሩ ይችላሉ፤ ይቅርታ አድርጉልኝ)።

ካለፈው የማይማር የድርጅት መሪ ወይንም የድርጅት ተከታይ ጠላት ቢያስረው፤ቢገርፈው፤ ቢያግዱት የሚታዘንለት አይመስለኝም።አንዳርጋቸው ጽጌ ያ ሁሉ ፕሮፓጋንዳ ሲሰራ፤ ኢሳያስን ሲያዳምቅ፤ የማይገባውን የማይመስል የውሸት ተክለሰውነት ሲቀባባው "ተው" እየተባለ፤ አልሰማ ብሎ፤ በዛው በኩል መሞከር እራስን ለሞት መዳረግ ነው ተብሎ በቀድሞ የአርበኞች ግምባር መሪዎች እና ጋዜጠኞች ተው አትሂድ ሲሉት፤ "ውሸታሞች ናችሁ፤ባለ 5 ኮከብ ያለበት መስተንግዶ ነው እየተደረገልን ያለው፤ድህንነታችን የተጠበቀ ነው..." እያለ ስለ ኢሳያስ ፕሮፓጋንዳ እየሰራ ቅዠት ውስጥ ገብቶ፤ መጨረሻው አልሰማችሁም ብሎአቸው፤ እራሱን ወጥምድ ውስጥ አስገባ። የሚገርመው ደግሞ 'ጻረ አማራነቱ" በሽታው ስላልተወው ወያኔ እስር ቤትም ሆኖ ተናገር ሳይባል ሆላንድ ውስጥ ስለሚኖሮው ዶክተር አሰፋ ነጋሽን እየጠቀሰ ለማሳነስ ሲሞክር ማድመጤን እጅግ ገረመኝ። በጣም፤በጣም አስገራሚ!!! ዶክተር አሰፋ ነጋሽ አንዳርጋቸውን እስር ቤት ያስገባው ይመስል የአሰፋን ስም የመጥራት ቅዠቱ በ ቪዲዮ ሳዳምጥ ፤ ስለ አሰፋ ነጋሽ የነበረው ውስጣዊ ጥላቻ፤ ሳስበው አንዳርጋቸው መንግሥት ቢሆን ኖሮ የዶክተር አሰፋን "ሰቆቃ ውስጥ" አስገብቶ ምንኛ ስጋውን ዘልዝሎ በተለተለው የሚል አንዳች ነገር ነብሴን በፍርሃት ወረረው። ይህንን ጉድ የሚጠብቅ ሰው ነበር ብላችሁ ተዘጋጅታችሁ ታውቃላችሁ? እነኚህ ነበሩ መካራን ተቋቁሞው ነፃነት ያመጣሉ ሲባልላቸው የነበሩት!

ዶክተር ታዬ ወለደሰማያትን የወለደች እናት እሱን ወልዳ መምከንዋ ምንኛ በደለችን እናንተዬ!? አየ ማንዴላው አንዳርጋቸው!

"ቢመከሩኝ ቢመከሩኝ አልሰማ ብየ ሱኳር ስልስ ተይዤ....." ያለው ማን ነው "ታምራት ላይኔ" ነው መሰለኝ።

ትግሬዎች "ዝመጽእ ክትፈልጥ ዝሓለፈ ኣስተውዕል" (የሚመጣውን ለማወቅ፤ ያለፈውን አስተውል" ይላሉ።

አረ ሌላም አለ “ዕድሚኡ ዝሓጸረ በጊዕ ኣብ እንዳ ተኹላ የውግዕ” (ዕድሜው ያጠረ በግ፤ ተኩላዎች ቤት ሄዶ ያወጋል/ይጫወታል/ይዝናናል)። የግንቦት 7 እና የፋሺስቱ ኢሳያስ ወዳጅነት ኢትዮጵያን ነጻ ያወጣል ብለው የሚሞኙ ሰዎች አንድም ኤርትራን/ኢትዮጵያን ለ30 አመት ያናጉዋት ግለሰቦች እና ሕዝቡ ኣያውቁትም ወይንም እንደ እነ “ኤፍሬም ማዴቦ” የመሳሰሉ እንደ ነገሩን “ኤርትራ 14ኛዋ ክፍለሃገራችን ነች! እያሉ የሚያደነቁርዋችሁ፡ ዓሰብ! ዓሰብ! የሚሉ አማራ ነፍጠኞችን እዚሁ በኛ አካባቢ የሚገኙትን በቁጥጥራችን ስር አድርገንላችኋል፤ጥርጣሬ አይግባችሁ....ይህ ንግግር የድርጅቴ ፖሊሲ እና ድርጅቴን ወክየ ነው እየተናገርኩ ያለሁት....” ብሎ ኦክላንድ ድረስ መጥቶ ድርጅቱን በመወከል ኤርትራዊያን ፋስቲቫል ተገኝቶ ኑዛዜው እንደገለጸላቸው ሁሉ፤ ግልጽ የሆነ የግንቦት 7 ዓላማ፤ የኤርትራን ሕልምና ፍላጎት በጠመንጃ ባሸከርነት ለማስፈጸም እያወቁ ወደ ኤርትራ የሚሄዱ ካልሆኑ በስተቀር፤ ወይንም እንደ እነ ‘አነግ እና ኦብነግ’ ለግንጣላ ስራ አግዙን የሚል ካልሆነ ሌላ ጤነኛ ሰው ካለፉት ሰዎች ማስጠንቀቂያና ምክር ንቆ ወደ ኤርትራ ሄዶ ድረጅት የሚመሰርት ጤነኛ ሰው ነው ብለህ ለመገመት ያስቸግራል።

ደጋግሜ እንደገለጽኩት ብርሃኑ እና ንአምን በኢሳያስ አፈወርቂ ታጠቁ አልታጠቁ ወደ ኤርትራ ሄዱ አልሄዱ እኔ የማየው ድረጅታቸው የሚከተለውን ፖሊሲ ነው። ፖሊሲያቸው እና እምነታቸው ደግሞ “ኤፍሬም ማዴቦ” በግልጽ ባደባባይ በቪዲዮ እየተቀዳ ድርጅቱ የሚከተለው መተከል/መስምርና የሚያምንበት መመሪያው ሳይደብቅ ነግሮናል።አሁን ወደ ኤርትራ ዘልቀዋል የተባሉት መሪዎች ናቸው የሚባሉት የግንቦት 7 ሁለት መሪዎች፤ ወደ ኤርትራ መሄድ ከነበረባቸው ድሮ ሲመሰረት ነበር። አሁን ከኛ ጠንካራ ትችት ሲሰነዘርባቸው የነበረው ፈተና/ቻለንጅ ፤ሲጠነከርባቸው፤የታጠቀን ድርጅት እምራለሁ እያልክ ውጭ አገር ስራ እሰሩ እንዲህ ማላገጥና መዝለቅ ስለማይቻል፤ በፈራ ተባ፤ ጨክነው ሄደዋል። መሄዳቸው ያስመሰግናቸዋል። ሆኖም፤ ሄዱ አልሄዱ ለኔ ምንም ማለት አይደልም።

ብርሃኑ፤ ንአምን፤ ኤፍሬም ማዴቦ የሚከተሉት ፖሊሲ፤ ለወደፊቱ ለማስፈጸም ያቀዱት እና ፍላጎታቸው፤ ስለ ኤርትራ ያላቸው፤ስለ ድምበራችን እና ብሄራዊ ክብራችን የሚከተሉት ‘መስመር’ ነው ለኔ የማንነታቸው ሚዛን የምመዝነው። ምላሳቸው የሚሰነዝረው ንግግር አስተውየ ነው የተቃወምኳቸው። ለዚህም ታጠቁ አልታጠቁ ኤርትራ ሄዱ አልሄዱ መስመራቸው ከወያኔ እኩል ነው።

ኤርትራ ውስጥ እነሱን አምነው ለመታገል የሄዱትን ሰዎች ደብድበዋል፤ አሰቃይተዋል፤ አስገድለዋል፤ እነሱን አምነው ወደ ኤርትራ የሄዱ ወጣቶች ደም አምባ አስለቅሰዋቸዋል፤ በጨካኞች

እንዲዋረዱ አስመርረዋቸዋል፤ ከኑሮአቸው አፈናቅለዋቸዋል። ይህ እያወቀ ግንቦት 7ን የሚከብ ሰው ሁሉ ለሰው ልጅ ክብር አለኝ ቢል፤ ውሸት ነው።

ከዚህ ወንጀል ሌላ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ጎሳ/ሕዝብ በድምጽ በሬፈረንደም ልገንጠል የሚል ካለ ለውይይት አቅርቦ በአብላጫ ደምጽ ካለፈ "መገንጠል መብቱ ነው"፤ በጠምንጃ አንይዘውም፤ "የዲሞክራሲ ትርጉሙ ያ ነው' ብሎናል ብርሃኑ እራሱ ባንደበቱ፤ ባደባባይ ሲናገር (ፖሊሲ የለንም ይላሉ፤ ፖሊሲያቸው ይህ ነው)።በትጠይቁት እሱም አይክደውም። (በሌላ አነጋገር የእነ ብርሃኑ ዲሞክራሲና ወደ ኤርትራ መጓዝ "ለአገር ማፍረሻ መጠቀሚያ ዘዴ" የተቀመመ ሴራ ነው ማለት ነው)። ይህ ሁሉ ወንጀል የተሸከመ አስፈሪ ቡድን፤ ከወያኔም ከሻዕቢያም ለይቼ አላየውም።

የኢሳት ጋዜጠኞችና "አክቲቪስት" የሚባሉ ሰዎች ማወቅ ያለባቸው፤ የገዛ ታጋዮቹን በኤርትራ ገራፊዎች እንዲሰቃዩ ያደረገ አንዳርጋቸው ጽጌ "የኔ አምበሳ" ብሎ ሽልማቱን አውልቆ ለአንዳርጋቸው ጽጌ ሸላሚው "ታማኝ በየነ" እና "ሲሳይ አገና" በድርጊታቸው ማፈርና ይቅርታ መጠየቅ ይገባቸዋል። ለሰው ልጅ መብት ቆመናል እያሉ "የወያኔን ግፍ እያጋለጡ" የቅርብ ጓዶቻቸው በዜጎቻችን ላይ ወንጀል ሲፈጽሙ እና ሰውን ስያስለቅሱ ግን 'ሽልማት መሸለም" "እንዳይናገሩ መድረክ መንፈግ" እጅግ የከፋ የወንጀል ተባባሪነት ነው። ከዚያም አልፎ ከሃዲነት ነው። የተናገሩትን መስለው አለመገኘት ደግሞ ከቶ አሳአፈሪ ነገር የለም።

እኔ ያስገረመኝ እና ያስፈራኝ ግን፤ ምሁራኖችና ጋዜጠኞች ለዚህ ድረጅት ሙሉ ልባቸው ሰጥተው ሳያፍሩ በግልጽ ድጋፋቸው ብቻ ሳይሆን፤ ከሚገባ በላይ ውሸትን እያገዘፉ ከኤርትራኖች የቀሰሙትን "ውሸትን የማግዘፍ" ባህል ከመቸው አንደተማሩት ባይገባኝም፤ በጣም አስፈሪ በሆነ ፍጥነት የፕሮፓጋንዳ አሎሎአቸው ሳያስተውሉ 'ነገ ምን ይከሰት ይሆን' ሳይሉ በዓይነ ዕውርነት መወርወራቸው ግዙፍ አስፈሪ ጭራቆች ሆነው እየመጡ ናቸው። ምክንያቱም ምሁራንና ጋዜጠኞች 'ካልት" ገምቢዎች ከሆኑ መላውን ሕዝብ ወደ "በግነት" የመቀየር ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል።በግ ደግሞ ከተኩላ ቤት ዘው ብሎ ገብቶ መዝናናትን ይለምድ እና እራሱን እና አገሩን ለተኩላ መንጋ ያጋልጣል።

መቸ ይህ ብቻ! ምሁራኖቹ እና ጋዜጠኞቹ (የኢሳት ጋዜጠኞችን በምሳሌ ውሰዱ) ከላይ በጨረፍታ የጠቀስኩት ሲሳይ አገና የተባለው በደርግ ጊዜ ድሮ የመቶአለቃነት ማዕረግ ነበረው የሚባለው ጋዜጠኛ፤ ከነበረው የክብር መድረክ ወርዶ፤ ለብርሃኑ ነጋ ፕሮፓጋንዳ ማደሩ እና ስለ ኤርትራው ነብሰገዳይ ስለ ኢሳያስ አፈወርቂ ስርዓት አንዲትም ቀን ብትሆን እንደ ጋዜጠኛነቱ በመድረኩም ሆነ በፖለቲካ መነጋገርያ ትንተና ክፍለጊዜ አንዳይነሳ አድርጎ 'ከርችም' አድርጎ መዝጋቱን ልብ በሉ።

እንዲሁም በወዳጁ በአንዳርጋቸው የተቀጠቀጡትን ሰለባዎች “ወያኔዎች” ናቸው እየተባለ በመድረካቸው ሲሰበክ፤ አንዳርጋቸው ጽጌ አሰቃይቶናል፤ ለኤርትራ ገራፊዎች አሳልፎ ሰጥቶናል፤ “እምቢ ካልክ ለነሱ ነው አሳልፌ እንድትገርፍ የማደርግህ” ብሎናል፤ ከብርሃኑም ሆነ ከአንዳርጋቸው ወይንም ከግንቦት 7 አመራሮች ከኛ ጋር ጋብዛችሁ የተፈጸመብንን ግፍ ሕዝብ እንዲያውቀው ፊት-ለፊት ኢሳት ላይ አነጋግሩን፤ ሕዝብ ይፍረደን፤ ግንቦት 7 ወንጀለኛ ነው..... ብለው ሲሉ “ሲሳይ እና መሰል ጋዜጠኞቹ” የተጻፈላቸው ደብዳቤ ቀዳድደው ጥለው፤ ሰምተው እንዳልሰሙ፤ ከነዚህ ሰለባዎች የተጻፈላቸው ድብዳቤ አንብበው እንዳላነበቡ “ጀሮ ዳባ” ብለው ለግንቦት 7 ወግነው፤ የግንቦት 7 ወንጀል እንዳይጋለጥ አፍነው ደብቀው ከሚጓዙት አንዱ ሲሳይ አገና ነው። ለዚህ ነው ጋዜጠኞቻችን “ለነፃነት እንታገላለን ብለው ወደ ኤርትራ ሄደው በግንቦት 7 መሪዎች ውሳኔ የተገረፉትን እያሳነሱ ገራፊዎቻቸውን የሚያቆለጳጵሱ ማፍያዎችን የማቆላጳስ ስራ ውስጥ ገብተው “የማፊያ ጋዜጠኞች” ሆነዋል የሚያሰኘኝ ለዚህ ነው።

ይህ ጽሑፌን ካነበባችሁ በኋላ ይህንን አድምጡ፤

**_Ginbot 7 head of finance Shitaw Shiferraw talks about his ordeal in Eritrea** https://youtu.be/XW3kk7Ajhbk

ለአንድ ጋዜጠኛም ሆነ ለታማኝ በየነ የመሳሰሉ “አክቲቪስቶች” ይህ አውድዮ ላይ የሚደመጠው ልቅሶና እሮሮ ትልቅ ፈተና ነው። ሲሳይም ሆነ ታማኝ በየነ ይህንን ልቅሶና እሮሮ በዜጋ ላይ የተፈጸመ ወንጀል መሆኑን እያወቁ ለግንቦት 7 ወግነው፤ ቸል ብለው ሲያልፉት፤ እነኚህ አቤቱታ አቅራቢዎች ድምጻቸው አፍኖ በኢሳትና በመሳሰሉ ሕዝባዊ መድረኮቻቸው እንዳይደመጡ ማድረጉ፤ በሞራልም በመንፈስም፤በሙያ ተወቃሽነት ካላስፈራቸው ሌላ ምን ሊያስፍራቸው የሚችል ነገር አለ?

በተለይ ሲሳይ አገና የነኚህ ሰዎች እሮሮ አፍኖ በየ ራዲዮኑ እና መድረኩ እየተጋበዘ ‘ስለ ብርሃኑ እና ስለ አመራሮቹ አስመራ መዝለቅ “ምርቃንና ሙገሳን”..... መለፍልፍ” ካንድ ጋዜጠኛ ነኝ ከሚል ታዋቂ “አፈ ጮማ ጋዜጠኛ” የሚጠበቅ ነው? የወያኔ ጋዜጠኞችን እየወቅስክ፤ የሚሰሩትን የተወገዘውን የጋዜጠኛነት ባሕሪ መልሰህ እራስህ እየደገምክ፤ የራስህን ስራ ሳታጠናቅቅ እኛን የመውቀስ ሞራል የለህም ብለው የወያኔ ጋዘጠኞች ቢተቹት ምን ሊል ነው?

ሲሳይ አገና “ኢሳት” ከውጭ አገር ወይንም ከውጭ ሃይል ገንዘብ ዕርዳታ አግኝቶ አያወቅም ብሎ ሲዋሽ፤ የግንቦት 7 ቅጥረኛነት እና ውሸት አግዝፎ ማውራት ምን ይረባል? ከአንድ የውጭ አገር ምክትል ፕረዚዳንት (ሁለተኛው ሰው ከሆነው) ግማሽ ሚሊዮን ዶላር ባጀት

ተፈቅዶልናል። እርዳታውም በየስድስት ወሩ ግማሽ፤ግማሽ ሚሊዮን ዶላር ይሰጠናል፤ ከፊሉ ለእሳት ስራ ማስኬጃ ይውላል፤ እያለ፤ ዕርዳታ አግኝተናል እያለ ብርሃኑ በቃሉ እየተናገረ እያለ፤ ሲሳይ ግን ዓይኑን በውሸት መሃረም ጨፍኖ "አናጋኝም"፤ እሳት በሕዝብ ነው የሚደገፈው፤ እኛ የሕዝብ ዓይን እና ጆሮ ነን፡.... ማለት ምን ይባላል? የነ ሽታው ሽፈራው ዕምባ ለነ ሲሳይ ምኑ ነው? ምንም! ይህ ጉድ ደብቀው ነው የሕዝብ ጆሮ እና ዓይን ነን የሚሉን። እንዲህ ያለ ጋዜጠኛ በኢትዮጵያ ምድር አልታየም፣ ብሎ የሚል ምስኪን ጓደኛ አለኝ።እነኚህ ናቸው ጋዜጠኞች እየተባሉ የሚነገርላቸው ያሉት።

እስኪ ሲሳይ አገናን ጠይቁት፡ እነ ሽታው ኢትዮጵያዊያን ዜጎች አይደሉም ወይ ብላችሁ እስኪ ጠይቁት? ሲሳይ እና መሰሎቹ ለነ ሽታው ሽፈራው እና ስንታየሁና ጓዶቻቸው በሕዝብ ፊት "ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው" እላለሁ። ልክ ኤልያስ ክፍሌ በጥሩ መንፈስ "ይቅርታ እንደጠየቀን" ሲሳይ አገና እና መሰል ጓዶቹ እንዲሁም ታማኝ በየነ ጨምሮ፤ 'ለነዚህ ሰለባዎች እና ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ሕዝብ ጭምር ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው"።

እነኚህ ጋዜጠኞች  ወደ ሂትለሩ ጆሴፍ ጎብልነት ሊቀየሩ ምንም የቀራቸው ባህሪ የለም ማለት ያስችላል። ውሸት እየገዘፈ ሲነገር፤ ሕብረተሱ ይበልጥ እያመነው ይሄድ እና መጨረሻ እውነት መስሎት ይከተለዋል። ብዙ ጅል ምሁር ሰሞኑን ፖለቲካው ያልተረዳው ደንቆሮውን አባዝተው አራብተው  በየፓልቶኩ በውሸት ጩቤ እያስጮኹት ነው። ፓልቶክ ስትገቡ የንቃተ ሕሊናው ዝቅጠት እጅግ ያሳስባል። "ምንሊክ አዳራሽ" ሓሙስ አንገባለን ፤ አዘዞ ደርሰናል፤ እንዲል በስሜት አስከረውታል። ባዶ ሜዳ ላይ! ለዚህ ደግሞ ተጠያቂዎቹ እነኚህ "ጋዜጠኞች ነን የሚሉን ኢሳት እና መሰል ጋዜጠኞች ናቸው።

ሕብረተሰቡ በእነኚህ ጋዜጠኞች ላይም ዓይኑን መግለጥ አስፈላጊ ነው። ተቃዋሚ ጋዜጠኞች "አብዛኛዎቹ" የልተመረጡ "ንጉሶች" ሊያነግሱብን እየተሯሯጡ ናቸው የምለው ለዚህ ነው። እነኚህ ጋዜጠኞች በውሸት ኤርትራዊያንን ሊቀድሙ የቀራቸው ነገር የለም።

መች ይህ ብቻ፡ ኢሳያስን እኮ ነው "ክቡር ፕረዚዳንት ኢሳየስ" እያሉ የሚጠሩት እና ቃለ መጠይቅ የሚያቀርቡለት እና የሚሽኮረመሙለት! እስኪ በወዳጃቸውና አማካሪያቸው በጦቢያው ጋዜጠኛ አቶ ጸጋዬ ገብረመድህን አርአያ ልዋስ እና ስለ እነዚህ መሳይ ጋዜጠኞች ጠላትን የማሞካሸት ባሕሪ አስከፊነት በጦቢያ መጽሄት ላይ ምን እንዳሉ ልግለጽ፤

" ዚያድ ባሬን ከፍ ዝቅ አድርገን ስንዘልፋቸው ለቆየነው ሁሉ የኦጋዴንን ወረራ በወገናችን ላይ የደረሰውን ጭፍጨፋና እልቂት ረስተን "ክቡር ፕረዚዳንት ዚያድ ባሬ" ለማለት አላስቸገረንም" ይላሉ። እውነት እውነት ! እነ መሳይ መኮንን፤ ፋሲል የኔ አለም (ወንድሞቻቸው ወደ ግንቦት 7 ወደ ኤርትራ እንዳይቀላቀሉ የመከሩ- ያንን እያዘጋጀሁ ነው አልረሳሁትም፤ጊዜ እየተጣበበብኝ ስለሆነ ነው፤አስነብባችኋለሁ 'ጠብቁኝ') ወደ ኤርትራ

መሄድ ብቻ ሳይሆን እነዚህም ‘ክቡር ፕረዚዳንት ኢሳያስ’ እንዳነጋገርናቸው፤ እያሉ ነው ፤ ጠላታችንን በክቡርነት እያመጻደቁልን ያሉት። ይህ እንዳይበቃ፤ ሰማይ ተሰበረ፤ ወያኔ አለቀለት፤ የወያኔ ወታደር ረፈረፋት፤ አዘዞ በር ደረሱ፤ ጎንደር ደረሱ፤ እያሉ ይዋሻሉ። ይህ ውሸት ከየት እንደቀዱት የታወቀ ነው። አባባ የተባለችው የድሮ የኤርትራ ሻዕቢያ ጋዜጠኛ እንደነገረችን.........

በክፍል ሁለት ይቀጥላል፤.......

ማሳሰቢያ፤

ጽሑፌ ከመደምደሜ በፊት፤ ባለፈው ሰሞን በተቸሁት ሳምንታዊ ጽሑፌ ውስጥ እርማት ለማድረግ እፈልጋለሁ።ዜናነህ መኮንን የተባለው እስራሎች አገር የሚኖር የይሁዲዎች ጉዳይ ለኛ ለይሁዲዎች ተውት፤ አያገባችሁም የሚለን ይህ የጥንት ጋዜጠኛ፤ “ጥርስ የገባች አገር” የሚለው መጽሐፍ ስፔንሰር ሳይሆን ሌቪን ነው ያለ መስሎኝ በስህተት አርሜው ነበር። ሆኖም በዛው ላይ አልተሳሰተም፤ እርማት ይደረግለት። አሁን ባለው ጋዜጠኛነት ከቀጠለ ግን ብዙ አመት ያገለገለበትን ሙያው በቃኝ ብሎ ቢሰናበት ይሻላል እላለሁ። ፍጹም እየተባለሸበት ሄዷል እና። ስለ ግንቦት 7 ጉዳይ በክፍል ሁለት እንገኛኝ።
አመሰግናለሁ፡-
ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ) getachre@aol.com